አንድ ሰዉ ሙስሊም ሊሆን ዘንድ

1) በጣዖት መካድ 2) በአላህ ብቻ ማመን እንደሚገባው ተማምረናል።

ቀጥሎ ደግሞ :-

- ጣዖት ምንድን ነው?
- በጣዖት እንዴት ነው የሚካደው?

ስለሚለው ነጥብ እንማማራለን።

★ **ጣዖት ማለት** :- ከአላህ ውጭ የሚመለክ ፤ በመመለኩም የሚወድ (የሚደሰት) ማንኛውም ነገር ነዉ።

ይህ ሲባል :- በመመለካቸው የማይወዱ ወይም እንዳይመለኩ የሚያስጠነቅቁ ሰዎች እና መላኢኮች ጣዖት አይባሉም።

ለምሳሌ : (ጅብሪል ፣ ነብዩ ዒሳ ፣ መርየም ፣ ነብዩ ሙሀመድ) እና ሌሎች ደጋግ ሰዎች ወይም መላኢኮች ጣዖት አይደሉም። ምክንያቱም እንዲመለኩ አይፈቅዱም። አምልኩን እያሉም አልተጣሩም። እነሱን ያመለከ ሰው በትክክል የተገዛው ሸይጧንን ነው። ምክንያቱም ወደ ጣዖት አምልኮ የሚጣራው ሸይጣን ነዉ።

ከእነዚህ ዉጭ የሆነ አካል ሁሉ ሲመለክ ጣዖት ይባላል።

📖የጣዖት አይነቶች ብዙ ናቸው።

ከተለያዩ ቅርፃ ቅርፅ የተጠረቡ ሊሆኑ ይችላሉ። ሰው ወይም ጂን ሊሆን ይችላል። እንስሳ ሊሆንም ይችላል።

በዓለማችን ላይ ያሉ የጣኦት አይነቶች በጣም ብዙ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ 5 ናቸው።

1ኛ :- ሸይጧን ነው። ከአላህ ሌላ ያሉ አካሎች እንዲመለኩ ይጣራል።

2ኛ :- የሩቅን እውቀት አዉቃለሁ የሚል ። ለምሳሌ :- ጠንቋይ ፣ አስማተኛ ፣ ኮከብ ቆጣሪ ፣ የቡና ሲኒ ወይም መዳፍ የሚያነቡና የመሳሰሉት

3ኛ :- እኔን አምልኩኝ እያለ ወደ ራሱ አመልኮት የሚጣራ ሰው።

4ኛ :- አላህ ያልፈቀደዉን ህግ የሚያወጣ መንግስት ፣ ፓርላማ ፣ ዳኛ እና የመሳሰሉት

5ኛ :- ከአላህ ህግ ዉጭ በሌላ ህግ የሚፈርዱ ሰዎች እና በዙሪያቸዉ ያሉ አጋዦቻቸው

እነዚህ ዋና ዋና የጣኦት አይነቶች ሲሆኑ የዘመኑ ማህበረሰብ እነዚህንና የተለያዩ የጣዖት አይነቶችን እያመለከ ይገኛል። እንደዉም በዘመናችን ክህደት ከመብዛቱ የተነሳ ሰይጣንን በግልፅ የሚያመልኩ ካፊሮች የመጡበት ዘመን ላይ ደርሰናል።

በሁሉም ሀገራት ላይ ያሉ መሪዎችም እየተመለኩ ነው። አላህ ያልፈቀደውን ህግና ስርዓት እያወጡ ህዝብን ይመራሉ። ህዝቦቻቸዉም ይከተሏቸዋል። ትእዛዛቸዉን ይቀበላሉ። በዚህ አደገኛ ክህደት ላይ የወደቀዉ የዘመኑ ህዝብ ክርስቲያን ወይም አይሁድ ብቻ ሳይሆን ሙስሊም ነኝ እያለ የሚሞግተዉ ሙሽሪኩ ህዝብም ጭምር ነው።

ለምሳሌ :- ሳዉዲን ፣ ግብፅን እና ሌሎቹን የአረብ ሀገራት መጥቀስ እንችላለን። በስም ደረጃ ሙስሊም ነን ይላሉ። ይሰግዳሉ። ሃጅ ይፈፅማሉ። ላኢላሃኢሏህ ይላሉ። ግን በየትኛዉም ጣዖት አይክዱም!!!!

📖 ሰዎች ወደ ጣዖት አምልኮት እንዴት ይገባሉ???

ሰዎች ወደ ጣዖት አምልኮት የሚገቡት ከሶስት መንገዶች በአንዱ ነው።

1ኛ በመከተል :-

አንድ ሰው ከቁርአንና ከሀዲስ ውጭ በሆነ መመሪያ እመራለሁ ቢል ጣዖት ይሆናል። እሱን መከተል ደግሞ ጣዖትን ማምልክ ማለት ነው።

ምክንያቱም ከአላህ ህግና መመሪያ ውጭ የማንንም ህግና መመሪያ እንዳንከተል አላህ አስጠንቅቋል።

በቁርአኑ ውስጥ አላህ እንዲህ ይላል ፦

ٱتَّبِعُواْ مَآ أُنزِلَ إِلَيۡكُم مِّن رَّبِّكُمۡ وَلَا تَتَّبِعُواْ مِن دُونِهِۦٓ أَوۡلِيَآءَۗ قَلِيلٗا مَّا تَذَكَّرُونَ

(ከጌታችሁ ወደእናንተ የተወረደውን ተከተሉ። ከአላህም ሌላ ረዳቶችን አትከተሉ። ጥቂትን ብቻ ትገሰጻላችሁ።)

የዘመናችን ከባዱ የጣዖት አምልኮ አዋቂዎችን ፣ የሀገር ሽማግሌዎችንና የእድሜ ባለፀጋዎችን በመከተል የሚከሰት ነው። ከቁርአን ጋር የማይስማማ ኃይማኖት እያስተማሯቸው በጭፍን ይከተሏቸዋል። ከመሆኑም ጋር ሙስሊም ነን ብለዉ ይሞግታሉ። አላህ እንዲህ ብሏል ፦

إِنَّهُمُ ٱتَّخَذُواْ ٱلشَّيَٰطِينَ أَوۡلِيَآءَ مِن دُونِ ٱللَّهِ وَيَحۡسَبُونَ أَنَّهُم مُّهۡتَدُونَ

سورة الأعراف, آية ٣٠

2ኛ ፦ **በመታዘዝ**

አንድ ሰው አላህ የፈቀደዉን ሀራም ቢያደርግ ወይም አላህ የከለከዉን ቢፈቅድ ጣዖት ይሆናል። ህግ የመደንገግ መብት የአላህ ብቻ ነው። ለሰዉ ልጆች መተዳደሪያ ስርዓት የማዉጣት ሀቅ የእርሱ ብቻ ነዉ። ይህን ሃቁን እወስዳለሁ ብሎ የሚከራከር ሰዉ ከአላህ ጋር እንዲመለክ እየሞከረ ስለሆነ ጣዖት ይሆናል።

በዚህ በኩልም ህዝባችን ከእስልምና ርቋል። በጣዖት አምልኮ ዉስጥ ታስሯል። የሀገር መሪዎችም ሆኑ የጎሳ መሪዎች በገዛ

ፍቃዳቸው ሃራም እና ሃላል እያሉ ህግ ያወጣሉ። ህብረተሰቡም ይታዘዛቸዋል። በዚህም ምክንያት ካፊር ሁነዋል።

ልብ እንበል!

ብዙ ሰዎች ጣኦት ማምለክ ሲባል (መከተል) እና (መታዘዝ) አምልኮት አይመስላቸዉም። ይህንንም ስለማይረዱ ከኩፍራቸው እንዲቶብቱ ሲጠየቁ .... እኛ አላጋራንም ፤ መቶበት አያስፈልገንም ሙስሊሞች ነን ይላሉ።

ነገር ግን ቁርአን እንደሚነግረን ከአላህና ከረሱል ዉጭ ያሉ አካሎችን መታዘዝም ሆነ መከተል አምልኮት መፈፀም ይሆናል። ረሱልን እንኳ የምንታዘዛቸው እሳቸው ፈጥረው ስለማይናገሩና የአላህን ትእዛዝ ስለሚያስተላልፉ ነዉ!!

3ኛ :- መንፈሳዊ አምልኮ መፈፀም

መንፈሳዊ አምልኮ በመፈፀም ወደ ጣዖት አምልኮ መዉደቅ በጣም የተለመደና በሰፊዉ የተስፋፋ የሽርክ ተግባር ነዉ።

ለምሳሌ :- ለቀብርና ለጂን ማረድ ፣ ወደ ጠንቋይ መሄድ ፣ የሞቱ ሰዎችን እርዳታ መለመን ፣ ለግዑዝ መስገድ እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። ይህ ተግባር ሽርክ መሆኑን የሚያስጠነቅቁ አንዳድ ሰዎች ሊያጋጥሙን ይችላሉ። ነገር ግን ሽርክ የሚፈፅሙትን ሰዎች ሙሽሪክ ለማለት ይቸገራሉ። ላኢለሃኢለሏህ ስላሉ ወይም ስለሰገዱ ብቻ ያሰልሟቸዋል። ሽርክ የሚሰሩት ስላላወቁ ነዉ ብለዉ ይከራከሩላቸዋል። ከነ ሽርካቸው ሙስሊም ያደርጓቸዋል። ይህ ራሱ

ተዉሂድን ያለማወቅ ችግር ስለሆነ እስልምናን የሚያፈርስ ነገር ነዉ።

በዚህ ነጥብ ዙሪያ እመለሰበታለሁ።ኢንሻአላህ!

*****

🧊 *በጣዖት ለመካድ 5 መስፈርቶች መሟላት አለባቸው።* 🧊

1ኛ ፡- ከአላህ ዉጭ የሚመለኩ ነገሮች ዉድቅ መሆናቸውን ማመን

2ኛ፡- እነዚያን አማልክቶች ከማምልክ መታቀብ

3ኛ፡- መጥላት

4ኛ፡-ጣዖት አምላኪዎችን ማክፈር

5ኛ ፡- ጣዖት አምላኪዎችን መጥላት

(ጠላት ማድረግ)

ማስረጃ ፡- (1)

قَدۡ كَانَتۡ لَكُمۡ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ فِيٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَٱلَّذِينَ مَعَهُۥٓ إِذۡ قَالُواْ لِقَوۡمِهِمۡ إِنَّا بُرَءَٰٓؤُاْ مِنكُمۡ وَمِمَّا تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ كَفَرۡنَا بِكُمۡ وَبَدَا بَيۡنَنَا وَبَيۡنَكُمُ ٱلۡعَدَٰوَةُ وَٱلۡبَغۡضَآءُ أَبَدًا حَتَّىٰ تُؤۡمِنُواْ بِٱللَّهِ وَحۡدَهُۥٓ

በኢብራሂምና በእነዚያ ከእርሱ ጋር በነበሩት (ምእምናን) መልካም መከተል አለቻችሁ። ለሕዝቦቻቸው «እኛ ከእናንተም ፣ ከአላህ ሌላ ከምትግገዙትም ንጹሖች ነን። በእናንተ ካድን። በአላህ አንድ ብቻ ሲኾን እስከምታምኑ ድረስ በእኛና በእናንተ መካከል ጠብና ጥላቻ ዘወትር ተገለጸ።» ባሉ ጊዜ (መልካም መከተል አለቻችሁ) ።

ማስረጃ ፡- (2)

لَّا يَتَّخِذِ ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلْكَٰفِرِينَ أَوْلِيَآءَ مِن دُونِ ٱلْمُؤْمِنِينَ ۖ وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ فَلَيْسَ مِنَ ٱللَّهِ فِي شَيْءٍ

ምእምናን ከሓዲዎችን ከምእምናን ሌላ ረዳቶች አድርገው አይያዙ፡ ፡ ይኼንንም የሚሠራ ሰው ከአላህ (ሃይማኖት) በምንም ውስጥ አይደለም።

-سورة آل عمران, آية ٢٨

ማስረጃ ፡- (3)

وَإِذْ قَالَ إِبْرَٰهِيمُ لِأَبِيهِ وَقَوْمِهِۦٓ إِنَّنِي بَرَآءٌ مِّمَّا تَعْبُدُونَ

ኢብራሂምም ለአባቱና ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ) ። «እኔ ከምትግገዙት ሁሉ ንጹሕ ነኝ።»

إِلَّا ٱلَّذِي فَطَرَنِي فَإِنَّهُۥ سَيَهْدِينِ

«ከዚያ ከፈጠረኝ በስተቀር (አልግገዛም) ። እርሱ በእርግጥ ይመራኛልና።»

-سورة الزخرف, آية ٢٧

****

📖 በአላህ (ሱ.ወ) ማመን

በአላህ ማመን ማለት ፦

- አላህ (ሱ.ወ) ከተጋሪ የጠራ ብቸኛ አምላክ ፣
- በስሞቹና ባህሪያቱ እንዲሁም በጌትነቱ ተወዳዳሪ ፣ አምሳያና ቢጤ የሌለው ጌታ መሆኑን ማመን
- አምልኮትን ለእርሱ ብቻ ጥርት አድርጎ (በኢኽላስ) መፈፀም
- እሱን በብቸኝነት የሚገዙ ሰዎችን መወዳጀትና በአላህ ላይ የሚያጋሩ ሰዎችን መጥላት ነው።

አላህ እንዲህ ይላል ፦

وَإِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ لَّآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلرَّحۡمَٰنُ ٱلرَّحِيمُ

«አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። (እርሱ) እጅግ በጣም ርኅሩህ አዛኝ ነው።»

በሌላም አንቀፅ እንዲህ ብሏል ፦

۞وَٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَلَا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـٔٗاۖ

አላህንም ተገዙ። በእርሱም ምንንም አታጋሩ።

እንዲህም ይላል፦

ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡحَقُّ وَأَنَّ مَا يَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ هُوَ ٱلۡبَٰطِلُ وَأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡكَبِيرُ

((ይህ አላህ እርሱ እውነት በመሆኑ ከእርሱም ሌላ የሚገዙት ነገር እርሱ ፍጹም ውሸት በመሆኑ አላህም እርሱ የሁሉ በላይ ታላቅ በመኾኑ ነው።)) {ሱረቱል ሀጅ: 62}

ትክክለኛው ወዳጅነት ለአላህ ፣ ለረሱልና ለአማኞች ብቻ መሆኑን ሲገልፅ እንዲህ ይላል ፦

إِنَّمَا وَلِيُّكُمُ ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱلَّذِينَ يُقِيمُونَ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ وَهُمۡ رَٰكِعُونَ

((ረዳታችሁ (ወዳጃችሁ) አላህና መልክተኛው እነዚያም ያመኑት ብቻ ናቸው። (እነርሱ) እነዚያ ሶላትን በደንቡ የሚሰግዱ እነርሱም ያጎነበሱ ኾነው ምጽዋትን የሚሰጡ ናቸው።))

በሌላም አንቀፅ እንዲህ ብሏል ፦

وَمَن يَتَوَلَّ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ فَإِنَّ حِزۡبَ ٱللَّهِ هُمُ ٱلۡغَٰلِبُونَ(سورة المائدة : ٥٦)

(አላህንና መልክተኛውን እነዚያንም ያመኑትን የሚወዳጅ ሰው (ከአላህ ጭፍሮች ይኾናል)። የአላህም ጭፍሮች እነርሱ አሸናፊዎች ናቸው።)

*****

በአላህ ማመንና የተዉሒድ ክፍሎች

በአላህ ማመን ይረጋገጥ ዘንድ በሶስቱም የተዉሒድ አይነቶች አላህን (ሱ.ወ) መነጠል ወይም ሶስቱንም የተዉሒድ አይነቶች ማረጋገጥ ይገባል።

እነርሱም ፦

1ኛ፦ **ተዉሂዱ ሩቡቢያህ**

ተዉሂዱ ሩቡቢያህ ማለት አላህን በጌትነቱ መነጠል ማለት ነዉ። ይህ የተዉሒድ ክፍል የአላህን (ሱ.ወ) ተግባራት የሚገልፅ ሲሆን የጌትነት መገለጫዎችን ለእርሱ ብቻ እንጅ ለማንም መስጠት ወይም ወደ ማንም ማስጠጋት አይቻልም።

ስለሆነም ኃያሉ ጌታ ብቸኛ ፈጣሪ ፣ ተንከባካቢ ፣ አስተናባሪ ፣ ረዛቂ ፣ ገዳይ ፣ ህያዉ አድራጊ ፣ አዛዥ ፣ ህግ አዉጪ ፣ ፈራጅ መሆኑን ማረጋገጥ ግዴታ ነው።

አላህ እንዲህ ይላል ፦

(أَلَا لَهُ ٱلْخَلْقُ وَٱلْأَمْرُ ۗ تَبَارَكَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلْعَٰلَمِينَ)

(ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው:: የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ::)

{አል-አህዛብ: 54}

ዓለምንና በውስጥ ያሉ ነገሮችን ሁሉ ያስገኘ እሱ ብቻ ሲሆን በዓለም ላይ ያሉ ነገሮችን ሁሉ የማስተናበር ፣ ለባሮቹ ህግና

መመሪያ የማዉጣት ፣ የማዘዝና የመከልከል ሙሉ መብትም የሱ ብቻ ነው።

በቀጣዩ አንቀፅ ደግሞ እንዲህ ይላል ፦

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱعۡبُدُواْ رَبَّكُمُ ٱلَّذِي خَلَقَكُمۡ وَٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ (سورة البقرة, آية ٢١-)

«እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጅላልና።»

በፍርዱ ተጋሪ ማድረግ እንደማይገባ የሚቀጥለዉ የቁርአን አንቀፅ ያስረዳናል ፦

(وَلَا يُشۡرِكُ فِي حُكۡمِهِۦٓ أَحَدٗا)

«በፍርዱ አንድንም አያጋራም።»

ለአላህ (ሱ.ወ) የሚገቡ የጌትነት መገለጫዎችን ያረጋገጠ ሰው አላህን ብቻ በአምልኮ መነጠሉ የግድ ይሆንበታል። ምክያቱም መመለክ ያለበት የሚፈጥር ፣ የሚረዝቅ ፣ የማይሞት ፣ ሙሉ ችሎታና አቅም ያለዉ አካል እንጂ ደካማ የሆነ ፍጡር አይደለም።

(هَٰذَا خَلۡقُ ٱللَّهِ فَأَرُونِي مَاذَا خَلَقَ ٱلَّذِينَ مِن دُونِهِۦۚ بَلِ ٱلظَّٰلِمُونَ فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٖ)سورة لقمان, آية ١١

(ይህ የአላህ ፍጡር ነው:: እነዚያ ከእርሱ ሌላ ያሉት ምንን እንደፈጠሩ እሰኪ አሳዩኝ:: በእውነቱ በዳዮቹ በግልጽ ጥመት ውሰጥ ናቸው::)

2) **ተዉሂዱል ኡሉሂያ ፦**

ተዉሂዱ ኡሉሂያ ማለት አላህን በአምላክነቱ መነጠል ማለት ሲሆን በየትኛውም የሚባዳ አይነት አላህን ብቻ መገዛት ግዴታ ይሆናል።

- በመንፈሳዊ የሚባዳ ተግባራት።
  ለምሳሌ ፦ (በዱዓ ፣ ሶላት ፣ በፆም እና በመሳሰሉት አላህን ብቻ መገዛት...
- በሁሉም የህይወት ጉዳዮች ወደ እርሱ ህግ ብቻ መፋረድ።
- የእርሱን ትእዛዝ ብቻ መቀበልና መመሪያዉን መከተል።

አላህ እንዲህ ይላል፦

وَإِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ لَّآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلرَّحۡمَٰنُ ٱلرَّحِيمُ

(አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም:: (እርሱ) እጅግ በጣም ርኅሩህ አዛኝ ነው::) {አል-በቀራህ: 163}

በሌላም የቁርአን አንቀፅ እንዲህ ይላል ፦

وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ لَعَلَّكُمۡ تُرۡحَمُونَ

(ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህንና መልክተኛውን ታዘዙ።) {አሊ-ዒምራን: 132}

- በአላህ ላይ ሌላን አካል በአምልኮት ያጋራ ሙሽሪክ ከሀዲ ይሆናል። ላኢላሃኢለሏህ ቢልም አትጠቅመውም። አለማወቁም ዑዝር አይሆነዉም።
- ከአላህ ሌላ ያሉ አካሎችን የታዘዘና የተከተለም እንደዚሁ ሙሽሪክ ይሆናል። ላኢላሃኢለሏህ ቢል አይጠቅመዉም። አለማወቁም ዑዝር አይሆነዉም።

3) **ተዉሂዱል አስማእ ወሲፋት ፦**

ይህ የተዉሒድ አይነት ደግሞ አላህን በስሞቹና ባህሪያቱ መነጠል ማለት ነው።

አላህ በርካታ ስሞችና ባህሪያት አሉት።

ባህሪያቱን ከፍጡር ባህሪ ጋር ማመሳሰል አይቻልም። ውድቅ ማድረግም አይፈቀድም። የእሱን አካኋን ለመገመትና ለመተንተን መሞከርም ኩፍር ላይ ይጥላል።

አንድ ሰው ሙስሊም ሊሆን ዘንድ ፈጣሪ ከፍጡር የሚለይባቸውን ወይም ጌታ ከባሮቹ የሚለይባቸውን ባህሪያት ማወቅ ይኖርበታል።

እነሱም ፦

1) አላህ ህያዉና ዘላለማዊ ነዉ።

2) ሁሉንም ነገር ያዉቃል። ዓለም ከመፈጠሯ በፊት የሚከሰቱ ነገሮችን ሁሉ አስቀድሞ አዉቆታል።

3) በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነዉ።

4) ሁሉንም ድምፆች ይሰማል።

5) ሁሉንም ክስተቶች ይመለከታል።

6) በፈለገው ጊዜና ሁኔታ ይናገራል። ቁርአንና ሌሎቹ መፅሀፎች የእርሱ ንግግር ናቸው።

7) ከፈጥረታት በላይ በዛቱ ከፍ ያለ ነዉ። አህባሾች እንደሚሞግቱት አላህ በሁሉም ቦታ ላይ የሰፈረ መንፈስ አይደለም!!

8) ስራዎቹ ሁሉ በጥበብ የተሞሉ ናቸው።

9) ሁሉንም ነገር ያስገኘና ባሮቹን የሚንከባከብ ነዉ።

እነዚህንና ከዚህም ዉጭ ያሉ የጌትነት ባህሪያቱን ማፅደቅ (ማረጋገጥ) ተገቢ ነዉ።

አላህ እንዲህ ብሏል ፦

قُلۡ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ * ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ * لَمۡ يَلِدۡ وَلَمۡ يُولَدۡ *وَلَمۡ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدُۢ

በል «እርሱ አላህ አንድ ነው። «አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። «አልወለደም፤ አልተወለደምም። «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።»

በሚከተለዉ የቁርአን አንቀፅ ደግሞ እንዲህ ይላል ፦

لَيۡسَ كَمِثۡلِهِۦ شَيۡءٞۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ

የሚመሰለው ምንም ነገር የለም። እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው።
። (ሹራ: 11)

በአሁኑ ዘመን ያሉ ካፊሮች (አላህ በሁሉም ቦታ ላይ ነው ያለዉ) ይላሉ። ይህን የሚናገር ሰው ካፊር ነዉ። እሱን ያላከፈረም ይከፍራል። ምክንያቱም አላህ ከዓርሽ በላይ እንደሆነ ነግሮናል። ከስድስቱ አቅጣጫዎች የጠራ ነዉ የሚሉትም አህባሾችና የነሱን መንገድ የተከተሉ ሰዎች ናቸው። አላህ ከፍጥረታት በላይ ነዉ።

አላህ አይናገርም የሚሉ አንጃዎችም በአላህ ላይ ዋሽተዋል። የአላህን ክብር ተዳፍረዋል። ግልፅ በሆነ ኩፍር ላይ ወድቀዋል።

በቅርቡ የመጡ ሰዎች ደግሞ አዲስ አባባል አመጡ። አላህ የሚሳነዉ ነገር ይኖራል ብሎ ማሰብ አያከፍርም ይላሉ። ከአላህ እዉቀት መደበቅ ይቻላል ብሎ መገመትም በጅህልና ከሆነ ዑዝር ይሰጥበታል ይላሉ። ይህ ሁሉ አባባል ግልፅ ጥመትና ክህደት ስለሆነ መጠንቀቅ ይገባል።